# የ COVID-19 ክትባቶች
# የተለመዱ ፍርሀቶች እና እውነታዎች

**ተጨንቄያለሁ...**

ክትባቱ COVID-19 ያስይዘኛል።

**እውነታ**

**ከክትባቱ COVID-19 ሊይዝዎት አይችልም።**

ክትባቶቹ COVID-19 የሚያስከትለውን የ COVID-19 ቫይረስን አይዙም።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

ክትባቶቹ ደህንነታቸው የተጠበቀ አይደለም እንዲሁም አይሰሩም።

**እውነታ**

**የ COVID-19 ክትባቶች ደኅንነታቸው የተጠበቀ እና ውጤታማ ናቸው።**

ክትባቶቹ በክሊኒካል ሙከራ ውስጥ በአስር ሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ተሞክረዋል። የድንገተኛ አጠቃቀም ፍቃድን ወይም ሙሉ ፍቃድን ለመደገፍ የሚያስፈልገውን የደህንነት፣ የውጤታማነት እና የምርት ጥራት ለማረጋገጥ የ FDA ን ፍጹም ሳይንሳዊ መስፈርቶች አሟልተዋል። ሰዎችን በ COVID-19 ከመታመም በመከላከል ረገድ ሁሉም በጣም ጥሩ ሆነው ተገኝተዋል።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

የ Johnson & Johnson ክትባት የጽንስ ህዋሳትን ይይዛል።

**እውነታ**

**የ Johnson & Johnson ክትባት የጽንስ አካሎችን ወይም የጽንስ ህዋሶችን አይይዝም።**

ክትባቱ እንደ ሌሎች ብዙ ክትባቶች ተመሳሳይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተሰርቷል። የክትባቱ አንዱ ክፍል ከ 35 ዓመታት በፊት በቀጠሮ ከተደረጉ ውርጃዎች ከተገኙ ሕዋሳት በላብራቶሪ ውስጥ እንዲጎለብቱ ከተደረጉ የህዋሳት ቅጂዎች የተሠራ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ ለእነዚህ ክትባቶች የሚያስፈልጉት የህዋስ አይነቶች ላብራቶሪ ውስጥ ተጠብቀው ቆይተዋል። ሌሎች ተጨማሪ የጽንስ ህዋሳት ምንጮች እነዚህ ክትባቶች ለመስራት ጥቅም ላይ አልዋሉም። ይህ ለተወሰኑ ሰዎች አዲስ መረጃ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ የፈንጣጣ፣ ሩቤላ እና ሄፓታይቲስ ኤ ክትባቶች በተመሳሳይ መንገድ የተዘጋጁ ናቸው።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

የ COVID-19 ክትባቶች መካንነት ወይም ስንፈተ ወሲብ ያስከትላሉ።

**እውነታ**

**ክትባቶቹ የእርስዎ የመራቢያ አካላት ላይ ተጽእኖ አያሳድሩም።**

ስነ ተዋልዶ እና ክትባት ላይ ያልዎትን ፍርሀቶች እንረዳዎታለን። የምናውቀውን እነሆ:- ክትባቶች መካንነት ወይም ስንፈተ ወሲብ እንደሚያስከትሉ የሚያሳይ ሳይንሳዊ ማስረጃ የለም። ክትባቱ ወደ ሰውነትዎ ሲገባ፣ የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ጸረ እንግዳ አካሎችን ለመስራት ከበሽታ የመከላከል ስርአትዎ ጋር ይሰራል። ይህ ሂደት የመራቢያ አካላትዎ ላይ ጣልቃ እንደሚገባ አይታወቅም።

**ተጨንቄያለሁ...**

COVID-19 ይዞኝ ከነበረ ክትባቱ አያስፈልገኝም።

**✔ እውነታ**

**COVID-19 ይዞት የነበረ ቢሆንም አሁንም ክትባት መውሰድ አለብዎት።**

ውሂቡ በበሽታው ከተያዙ በኋላ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ በ COVID-19 እንደገና መያዝ ያልተለመደ መሆኑን ያሳያል። ይህም ማለት ለትንሽ ጊዜ ከ COVID-19 የተወሰነ ጥበቃ (ተፈጥሯዊ በሽታ የመከላከል አቅም ይባላል) ሊኖርዎት ይችላል ማለት ነው። ሆኖም፣ ተፈጥሯዊ በሽታ የመከላከያ አቅም ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አናውቅም።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

ክትባቶቹ ሰዎችን የሚከታተሉ ማይክሮቺፖች አሏቸው።

**✔ እውነታ**

**ክትባቶች ማይክሮቺፕ ወይም የመከታተያ መሳሪያ አይዙም።**

ክትባቶቹ COVID-19 ን ለመከላከል ጸረ እንግዳ አካላትን ሰውነትዎ እንዲሰራ የሚረዱ ንጥረነገሮችን፣ እንዲሁም ቅባቶች፣ ጨዎች እና ስኳሮችን ብቻ ይይዛሉ።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

እርጉዝ ወይም አጥቢ ለሆኑ ሰዎች የ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝ አይደሉም።

**✔ እውነታ**

**የእርግዝና እና የወሊድ ህክምና ባለሙያዎች ለእርጉዞች፣ ለሚያጠቡ ወይም ለማርገዝ ላሰቡ ሰዎች የ COVID-19 ክትባትን እንዲወስዱ ይመክራሉ።**

መረጃዎች የ COVID-19 ክትባቶች በእርግዝና ጊዜ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ያሳያሉ። በእርግጥ አንዳንድ ጥናቶች ክትባት የወሰደች ወላጅ በእርግዝና እና ጡት በማጥባት የ COVID-19 ፀረ እንግዳ አካላትን እንኳን ወደ ልጇ ልታስተላልፍ እንደምትችል ያሳያሉ። ነፍሰ ጡር ሰዎች ሞትን ጨምሮ በ COVID-19 ለሚከሰት ከባድ በሽታ ተጋላጭ ናቸው። ክትባቶቹ ከሁሉ የተሻለ መከላከያ ናቸው።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

የ COVID-19 ክትባቶች የእኔን DNA ይለውጣሉ።

**✔ እውነታ**

**የ COVID-19 ክትባቶች DNA ዎን አይለውጡም ወይም አይጎዱም።**

አሁን ያሉት ሁሉም ክትባቶች COVID-19 ን ከሚያስከትለው ቫይረስ መከላከልን መገንባት ለመጀመር ለህዋሶቻችን መመሪያ ይሰጣሉ። ክትባቱ የእኛ DNA የሚቀመጥበት የህዋስ ክፍል ውስጥ አይገባም። ይልቁንም፣ ክትባቶቹ የበሽታ መከላከል አቅምን ለመገንባት ከሰውነታችን ተፈጥሯዊ መከላከያዎች ጋር ይሰራሉ።

---

**ተጨንቄያለሁ...**

ክትባት ከወሰድኩ በኋላ የደም መርጋት ያጋጥመኛል።

**✔ እውነታ**

**የደም መርጋት የማጋጠም እድሉ በጣም ዝቅተኛ ነው።**

ለምሳሌ፣ በየቀኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች ከሚወስዱት የወሊድ መቆጣጠሪያ ከሚመጣው የደም መርጋት ስጋት ይልቅ የማጋጠም እድሉ ዝቅተኛ ነው። ነገር ግን፣ ሊከሰት ከሚችል አደጋ የተነሳ የ Washington State Department of Health (DOH፣ የጤና መምሪያ) ከ Johnson & Johnson (J&J) ክትባት ይልቅ የ mRNA COVID-19 ክትባት (Pfizer-BioNTech ወይም Moderna) እንዲያገኙ ይመክርዎታል።

የ mRNA ክትባት መከተብ ካልቻሉ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ የ J&J ክትባት አሁንም ይገኛል። ስለ ስጋቶችዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።